# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

EthiOrthodox e-mail Outreach

## የኅዳር ወር ሁለተኛ ሰንበት

ከኅዳር ፯ እስከ ታኅሣሥ ፮ ወይም ፲፫ አስተምህሮ ይባላል። በዚህ ወር በአንደኛው ሳምንት ስለ አምላክ ቸርነት፣ ትዕግሥት፣ ክብር እና ምስጋና ለእግዚአብሔር ይቀርባል።

## የዕለቱ ምስባክ

ኢትዝክር ብነ አበሳነ ዘትካት
ፍጡነ ይርከበነ ሣህልከ እግዚኦ
እስመ ተመንደብነ ፈጽፉደ

የቀደመውን በደላችንን አታስብብን
ምህረትህ በቶሎ ይደረግልን
እጅግ ተቸግረናል።

መዝ ፸፰፥፰

ወንጌል፥ ማቴ ፮፥፭-፲፮
ቅዳሴ፥ ነአኲተከ (የጌታ ቅዳሴ)

## የዕለቱ ትምህርት

# የቀደመ በደላችንን አታስብብን

በቅዳሴ ጊዜ የተሰበከው መዝሙረ ዳዊት የቀደመ በደላችንን አታስብብን ምሕረትህ ፈጥኖ ይደረግልን እንጂ ይላል። እግዚአብሔር የቀደመ በደልን የማያስብ ወደ እርሱ የቀረቡትን ከበደላቸው የሚያነጻ ተነሳህያንን የይበቀል ኃዳጌ በቀል ነው። ዳዊት በሌላ ገጽ «ገባሬ ሣህል እግዚአብሔር - ይቅርታ አድራጊ እግዚአብሔር ነው» ይላል። በዚያው ክፍል «መሐሪ ወመስተሣህል እግዚአብሔር ርሁቅ መዓት ወብዙኃ ምሕረት ወጻድቅ - ይቅር ባይ መዓትህ የራቀ ምሕረትህ የበዛ እግዚአብሔር» ይላል። አሁንም የእግዚአብሔርን ምሕረት ተናግሮ የማይደክመው ዘማሪ «ሁል ጊዜ አይቀስፍም ለዘለዓለም አይቆጣም እንደ ኃጢአታችንም አላደረገብንም እንደበደላችን አልከፈለንም ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል እንዲሁ ምሕረቱን በሚፈሩት ላይ አጠነከረ ምሥራቅ ለምዕራብ እንደሚርቅ እንዲሁ ኃጢአታችንን ከእኛ አራቀ አባት ለልጆቹ እንደሚራራ እንዲሁ እግዚአብሔር ለሚፈሩት ይራራል።» ብሎ በሰፊው ምሕረቱን ዘመረው። ያሬድም በተዘጋጀው መዝሙር «ኢተዘኪሮ አበሳ ዚአነ ኢኃደገነ ፍጹመ ንማስን ኄር እግዚአብሔር - ኃጢአታችንን በደላችንን

## የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር

ኢተዘኪሮ አበሳ ዚአነ
(በደላችንን ሳያስብ) … (መዝሙር ዘአስተምህሮ)

**በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች**

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ሮሜ ፭፥፲ እስከ ፍጻሜ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ፩ኛ ዮሐ ፪፥፩-፲፫ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፳፪፥፩-፲፪ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

በማሰብ እንጠፋ ዘንድ ከቶ አልተወንም ቸር አምላክ …» ብሎ ከዳዊት ጋር የእግዚአብሔርን ምሕረት ያዜማል። አዎ በደልን ይቅር የሚል የርስቱንም ቅሬታ ዓመጽ የሚያሳልፍ እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም እርሱ ምሕረትን ይወዳል። ቁጣውንም ለዘለዓለም አይጠብቅም በነብዩ እንደተነገረ « … ተመልሶ ይምረናል ክፋታችንንም ይጠቀጥቃል በባሕሩ ጥልቅ ይጥለዋል።» (ሚክ ፯፥፲፰-፲፱)

የበደላችንን አድራሻ አጠፋው መድኃኒታችን በኃጢአታችን ላይ አላስኬደንም። እርሱ ጠቀጠቀልን በባሕር ትዕግሥቱ በባሕረ ምህረቱ ውስጥ ጣለልን። የኃጢአታችንንም አድራሻ ወደ ጥልቅ ባሕር በመጣል አጠፋው፤ በደላችንን የጠቀጠቀው ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እጆቹና እግሮቹ የቆሰሉት የእኛን በደል ሲረግጥ ነው። እርሱ በበደላችን ላይ አልፎ እኛን በአረፋት መስክ አሰማራን። በእውነት መንፈስ ከዳዊት ጋር «… ኃጢአትየ ዘበንእሲየ ወዕበድየ ኢትዝክር ሊተ እስመ ኪያከ ተወከልኩ - በልጅነቴ የሠራሁትን ኃጢአቴን አታስብብኝ አንተን አምኜለሁ አልፈር» እያልን እንዘምር (መዝ ፳፬፥፯) ምሕረቱንም « … እስመ ኃጢአተኑ ትትአቀብ እግዚኦ እግዚኦ መኑ ይቀውም አቤቱ - ኃጢአትንስ ብትጠባበቅ አቤቱ [በፊትህ] ማን ይቆማል?» እያልን እናድንቅ። በእውነት «መተላለፍ የቀረችለት ኃጢአቱም የተከደነችለት ምስጉን ነው። እግዚአብሔር በደልን የማይቆጥርበት በመንፈሱም ሽንገላ የሌለበት ምስጉን ነው።» (መዝ ፴፩፥፩)

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር … አሜን።*

ከመምህር ልዑል ቃል አካሉ ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ፩ኛ መጽሐፍ የተወሰደ

EthiOrthodox e-mail Outreach EthiOrthodox@AOL.COM